NHS England

NHS Leicestershire Partnership NHS Trust

**የዩኒቨርሲቲ ትምህርት እና ጥናት-ነክ ድርጅት**
ብሪጅ ፓርክ ፕላዛ
ብሪጅ ፓርክ መንገድ
ተርመስተን
ሌሲስተር
ኤል ኢ4 8ፒኪው

www.leicspart.nhs.uk

ሚያዚያ 2021

ውድ ታዳጊ ሰውእና ወላጅ/አሳዳጊ፣

**የታዳጊዎች ማጎልበቻ እና የማጅራት ገትር ክትባት መርሀ ግብር ለታዳጊ ልጆች**

እንደ ብሔራዊ ክትባት መርሀ ግብር አካል፣ የማህበረሰብ ክትባት አገልግሎታችን ለ9ኛ ክፍል (እድሜያቸው ከ 13 እስከ 14 አመት ለሆኑ) ታዳጊዎች በሙሉ 3 በ 1 የታዳጊዎች ማጎልበቻ እና የማጅራት ገትር ክትባት ይሰጣል። እነዚህ መደበኛ ክትባቶች ለመንጋጋ ቆልፍ፣ ተላላፊ የጉሮሮ በሽታ፣ የልጅነት ልምሻ (ቲ ዲ/አይ ፒ ቪ) እና ለማጅራት ገትር አይነቶች ለሆኑት ኤ ሲ ደብሊውእና ዋይ ይከላከላል። በአስራዎቹ እድሜም ሆነ ከዛ በላይ በሚሆኑበት ግዜ ከሁሉም የበለጠ መከላከያ ስለሚሰጥ ክትባቱን በዚህ እድሜመውሰድ አስፈላጊ ነው።

**አዎ, ክትባቱን መውሰድ እፈልጋለው**

**አይ, ክትባቱን መውሰድ አልፈልግም**

**ለአንድ ወይምለሁለቱምክትባቶች መስማማት ይችላሉ።**

**የትኛውንምእንደወሰኑ፣ ያሳውቁን።**

- ድህረ ገፃችን ላይ በመግባት የስምምነት ቅፁን በኦንላይን ይሙሉ፡ https://www.leicsandrutlandimms.co.uk/
- ተላላፊ የጉሮሮ በሽታ፣ መንጋጋ ቆልፍ እና የልጅነት ልምሻ (ቲዲ/አይ ፒ ቪ)፣ ማጅራት ገትር ኤ ሲ ደብሊውዋይ (9ኛ ክፍል ብቻ) የሚለውን ይምረጡ
- የትምህርት ቤትዎ ኮድ ያስፈልጋል።
- ለ **Winstanley School** የትምህርት ቤቱ ኮድ **LE143844** ነው
- ፎርሙሲገባ የማረጋገጫኢሜይል ይደርስዎታል።

*ወይምበቀጥታ ወደ ስምምነት ቅፃችን ለመሄድ ዘመናዊ ስልክዎን ካሜራ በመጠቀም ይህን የፈጣን መላሽ ኮድ መቃኘት ይችላሉ*

***ማሳሰቢያ፡*** *ኢሜይል አድራሻዎ ትክክል መሆኑን እና ከኢሜይል አድራሻውእና ከትምህርት ቤቱ ኮድ በፊትምወይምበኋላ ምንምክፍተቶች ወይምስርዓተ ነጥብ አለመኖሩን ያረጋግጡ።*



disability confident EMPLOYER

ይህ መልዕክት ወዲያውእንደደረስዎ የስምምነት ቅፁን ሙሉ በሙሉ መሙላት ይጠበቅብዎታል።

ሀሳብዎን በማንኛውምሰዓት መቀየር ይችላሉ።

ለመዘጋጀት እንዲያስችለን ከ ክትባቱ አንድ ቀን በፊት ስርዓቱን ለግዜውልንዘጋውእንችላለን። ከ ክትባቱ ቀን በኋላ ስርዓቱ ወዲያውኑ ይከፈታል። ይህንን በኦንላይን መሙላት ካልቻሉ፣ እባክዎ ድጋፍ ለመጠየቅ በ 0300 300 0007 ይደውሉልን። ቅፁን ለመሙላት ከቡድናችን አንዳቸውመልሰው ሊደውልልዎ ይችላል።

ክትባቶቹ በላይኛው ክንድ እንደ ሁለት የተለያዩ መርፌዎች ይሰጣሉ። በታዳጊዎች ማጎልበቻ እና የማጅራት ገትር ክትባት መርሀ ገብር ውስጥ የምንጠቀመው ክትባቶች **ጄላቲን ወይም አልኮል የላቸውም።** .

ስለ ታዳጊዎች ማጎልበቻ እና የማጅራት ገትር ክትባቶች የታካሚውን መረጃ በራሪ ወረቀት ለማንበብ፣ www.tiny.cc/boosterleaflet ይጎብኙ፤ ስለ ብሔራዊ የክትባት መርሀ ግብር የበለጠ መረጃ www.nhs.uk/conditions/vaccinations ይጎብኙ።

ታዳጊ ልጆች ስለእነዚህ ክትባቶች እና ሌሎች የጤና ጉዳዮች www.healthforteens.co.uk/health/immunisation በመጎብኘት የበለጠ ማወቅ ይችላሉ።

ቡድኑ በትምህርት ቤት ውስጥ ክትባቶቹን ይሰጣሉ። ክትባቱን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መድረሱን ለማረጋገጥ ሁሉም ተገቢ የ ኮቪድ ደህንነት መስፈርቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ከሁሉም ትምህርት ቤቶች ጋር በቅርበት እየሰራን ነው።

አብሮዎት የሚኖር አንድ የቤተሰብ አባል ራሱን ያገለለ ከሆነ ወይም ክትባት በሚሰጥበት ቀን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምልክቶች ካለብዎት **እባክዎ አይሳተፉ።**

- **ከፍተኛ የሙቀት መጠን – ደረትዎ ወይም ጀርባዎ ሲነካ የትኩሳት ስሜት ከተሰማዎት**
- **አዲስ የማያቋርጥ ሳል – ይህ ማለት በተደጋጋሚሳል ጀምረዋል ማለት ነው።**
- **የማሽተት ወይም የመቅመስ ስሜትዎ ከጠፋ ወይም ከተቀየረ – ይህ ማለት ይህ ማለት የማሽቱ ነገሮችን ወይም ምንምነገር ማሽተት ወይም መቅመስ እንደማይችሉ ወይም ከተለመደው የተለየ ጣእም ሲያስተውሉ ማለት ነው።**

በዛን ቀን ከቀሩ፣ ክትባቱ የሚገኝበት ሌላ ተጨማሪ እድል ይሰጣል። ይህ ክትባት በሃኪምዎ በመደበኛ ደረጃ እንደማይሰጥ እባክዎ ልብ ይበሉ።

በትምህርት ቤት ውስጥ የክትባት ክፍለ ግዜውን ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቅ ካልቻልን ሌላ አማራጭ ቦታ መስጠት እንደሚያስፈልግ እንገነዘባለን። ጉዳዩ እንደዛ መሆን ካለበት አገልግሎቱ ሙሉውን መረጃ እንደሚሰጥዎ ያረጋግጥልዎታል።

ባለፉት 5 አመታት ውስጥ የመንጋጋ ቆልፍ፣ የተላላፊ ጉሮሮ በሽታ እና የልጅነት ልምሻ (ቲ ዲ/አይ ፒ ቪ) ክትባት የወሰዱ ከሆነ እስከ ሚቀጥለው ግዜ ድረስ ይህ ክትባት አያስፈልግዎትም ነገር ግን አሁንም ቢሆን የማጅራት ገትር ክትባት መውሰድ ያስፈልግዎታል። እያንዳንዱ ታዳጊ ሰው ተገቢነቱን ለማረጋገጥ ይገመገማል። የማህፀን ጫፍ ካንሰር ክትባት ለመውሰድ ግዜዎ ከሆነ ምናልባትም በአንድ ግዜ ሊሰጥ ይችላል እናም ሶስቱንም ቢወስዱ ጉዳት የለውም።

ክትባቱን ተከትሎ የተወሰኑ የድህረ-ክትባት መረጃዎች ከማህበረሰብ የክትባት አገልግሎት በኢሜይል ይላክልዎታል እና መረጃው በታዳጊው የኤን ኤች ኤስ የጤና መዝገብ ላይ ይዘመናል።

ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ወይም በክትባቱ ወቅት የሚፈለጉትን ተጨማሪ ድጋፎች ለመወያየት ከፈለጉ ቡድኑን በስልክ ቁጥር 0300 300 0007 (አማራጭ 1 ይምረጡ ከዛ አማራጭ 4 ከዛ አማራጭ 2) ወይም በኢሜይል communityimms@leicspart.nhs.uk ማነ ጋገር ይችላሉ። ክትባቶችን በምንሰጥበት ጊዜ ስልክ ጥሪዎች ከፍተኛ ናቸው እናም ጥሪዎ መልስ እንዲያገኝ ከፍተኛ ጊዜ መጠበቅ ሊኖርብዎት ይችላል። ለቡድኑ የድምፅ መልእክት የመተው አማራጭ ይኖርዎታል እናም መልሰን እንደውላለን።

ከትህትና ጋር፣

ዶክተር ቲም ዴቪስ
**የምር መራ እና ክትባት አማካሪ መሪ**
**ኤን ኤች ኤስ እንግሊዝ እና ኤን ኤች ኤስ ማሻሻያ – ሚድላንድስ**

ሱዛን ሊዘርላንድ
**የክትባት አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ**
**ሌሲስተርሸር ኤን ኤች ኤስ አጋር ድርጅት**

**የኦንላይን ስምምነት ቅፅ አሞላል ማስታወሻ**

ይጎብኙ፡ https://www.leicsandrutlandimms.co.uk/Forms/DTP

የኢሜይል አድራሻዎን ያስገቡና ያረጋግጡ

የትምህርት ቤትዎን ኮድ ያስገቡ፡ LE143844 እና ትምህርት ቤት ፈልግ የሚለውን ይጫኑ። የትምህርት ቤትዎ ስም መታየት አለበት።

***ማሳሰቢያ፡***

- የኛን ገፅ ለማግኘት ኢንተርኔት ላይ "ሌሲስተር ክትባት" ብለው መፈለግ ይችላሉ
- ኢሜይል አድራሻዎ ትክክል መሆኑን እና ከ ኢሜይል አድራሻው እና ከትምህርት ቤቱ ኮድ በፊትም ወይም በኋላ ምንም ክፍተቶች ወይም ስርዓተ ነጥብ አለመኖሩን ያረጋግጡ

**ክፍል 1፡ የታካሚው መረጃ እና የመገኛ ዝርዝሮች**

**የሚገኝ ከሆነ እባክዎን የልጅዎን የኤን ኤች ኤስ ቁጥር ያክሉ**

በሀኪምዎ ተመዝግበው ከሆነ ይህ ቁጥር ሊኖርዎት ይገባል። ለእያንዳንዱ ሰው የተለያየ እና ባለ 10 ቁጥር አኀዝ ሲሆን በህክምና ካርዳቸው ላይ ይገኛል። በማንኛውም የ ኤን ኤች ኤስ ወረቀት፣ መድሀኒት ማዘዣ እና የልጁ ቀይ መፅሀፍ –"የልጁ የግል ጤና መዝገብ" ላይ ይገኛል።

**ክፍል 2፡ የስምምነት ሰነድ**

ለጉንፋን ክትባት ፈቃድ ለመስጠት ይህንን ይሙሉ

**ክፍል 3፡ የህክምና ታሪክ**

የክትባት ታሪክን እና በክትባቱ ግዜ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ድጋፍ የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ይሙሉ።

**ታዳጊው ያለ እርስዎ ስምምነት ይህንን ክትባት ለመውሰድ ለራሱ ሊፈቅድ ይችላል እና የጤና ባለሙያዎች በእውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ የማድረግ አቅማቸውን ይገመግማሉ ፡ ፡**

**መረጃ ማጋራት፡** በትምህርት ቤት ውስጥ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ፣ ማሳወቂያ ይቀርብና መረጃው በልጅዎ ኤን ኤች ኤስ የጤና መዝገብ ላይ ይታከላል ፡ ፡

**በሌሎች ቋንቋዎች የጤና መረጃ ድጋፍ ለማግኘት, እባክዎ፡** https://www.nhs.uk/about-us/health-information-in-other-languages/ **ይጎብኙ**